# ጊዜያዊ የ COVID-19 የራስ ምርመራ መመሪያ

## የዲሴምበር 5፣ 2022 ለውጦች ማጠቃለያ

- እድሜያቸው ከ 2 አመት በታች ለሆኑ ህጻናት ግለ ምርመራዎችን ስለመጠቀም ተጨማሪ መረጃ
- የምርመራ ውጤትዎ ኔጌቲቭ ከሆነ ማድረግ ያለብዎትን በሚመለከት የዘመነ መረጃ

## መግቢያ

የ COVID-19 ስርጭት እንዲቀንስ ለመርዳት ምርመራ ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው። ምርመራ ማድረግ በበርካታ ሁኔታዎች ውስጥ ጠቃሚ ነው:-

- የ COVID-19 ምልክቶች ካለብዎት፣ በተቻለ ፍጥነት ምርመራ ማድረግ እና በ COVID-19 የበሽታ ምልክት ውሳኔ ንድፎች (ተጨማሪ ቋንቋዎች ይገኛሉ) ውስጥ ያሉትን እምጃዎች ይከተሉ።
- COVID-19 ላለበት ሰው ከተጋለጡ፣ ምርመራ ማድረግን ጨምሮ፣ COVID-19 ላለበት ሰው ከተጋለጡ ማድረግ ያለብዎት (ተጨማሪ ቋንቋዎች አሉ) የሚለውን ላይ ያለውን መመሪያ መከተል አለብዎት።
- ምንም እንኳን የበሽታ ምልክቶች ባይኖርዎትም እና COVID-19 ላለበት ሰው መጋለጥዎን ባያውቁም አንዳንድ ጊዜ፣ እንደ ጉዞ ያሉ፣ ለሚመጡ እንቅስቃሴዎች አስቀድመው ሊመረመሩ ይችላሉ።

በጤና እንክብካቤ አቅራቢ፣ በህዝብ ጤና የምርመራ ጣቢያ ሊመረመሩ፣ ወይም በቤት ውስጥ ወይም በሌላ በማንኛውም ቦታ ሊደረግ የሚችል **የግለ መሰብሰቢያ መሳሪያ** ወይም **የግል ምርመራ** መጠቀም ይችላሉ። እንዲሁም አንዳንድ ጊዜ የራስ ምርመራ "የቤት ምርመራ"፣ "የቤት ውስጥ ምርመራ" ወይም "ያለ ሃኪም ትዕዛዝ የሚደረግ ምርመራ" ተብሎ ይጠራል። በአሁኑ ጊዜ የሚገኙ ግለ-ስብስብ መሳሪያዎች እና ግለ ምርመራዎች የአሁኑን ኢንፌክሽን ለመመርመር ጥቅም ላይ ይውላሉ፣ ማለትም አሁን ምናልባት COVID-19 ቢኖርብዎት ወይም ባይኖርብዎትም። ከዚህ በፊት COVID-19 እንደነበረብዎ መረጃ አይሰጡም።

የግለ ስብስብ መሳሪያዎች እና ግለ ምርመራዎች በሃኪም ትዕዛዝ ወይም ያለ ሃኪም ትዕዛዝ በሚሸጥ (ያለ ሃኪም ትዕዛዝ) መድሃኒት ቤት ወይም የችርቻሮ መደብር ውስጥ ይገኛሉ። አብዛኛው የግል መድህን ሽፋን ባለው ሰው በወር 8 ግለ ምርመራዎችን መሸፈን ይጠበቅበታል (እንግሊዝኛ ብቻ)። እንዲሁም በግዛቱ ያሉ ቤተሰቦች በ Say Yes! COVID Test (አዎ ይበሉ! የ COVID ምርመራ) ኢንሼቲቭ አማካኝነት ከ Department of Health (DOH፣ የጤና መምሪያ) ነጻ የ COVID-19 ምርመራዎችን ለመውሰድ ብቁ ናቸው። ይህ ከፌደራል ተነሳሽነት በተጨማሪ ነው። ቤተሰቦች በአሁኑ ጊዜ በእያንዳንዱ ወር ሁለት ትዕዛዞችን ማዘዝ ይችላሉ፣ ይህም በወር እስከ 10 የሚደርሱ ነጻ ምርመራዎችን ያካትታል። ትዕዛዞች በኦንላይን በ Home (ቤት) - Say Yes! To Covid Test (sayyescovidhometest.org) (ተጨማሪ ቋንቋዎች ይገኛሉ) ወይም በ DOH የ COVID-19 የስልክ መስመር 1-800-525-0127 ሊቀርቡ ይችላሉ። አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ለመመርመር መዘጋጀት እና ምርመራዎችን ማግኘት መቻል አስፈላጊ ነው። በአጠቃላይ ምርመራዎች ትዕዛዙ ከደረሰ፣ ከ 2-4 ባሉት ቀናት እንዲደርሱ መጠበቅ ይቻላል፣ ይሁን እንጂ ይህ በተለያዩ የግዛት ክፍሎች ሊለያይ ይችላል።

በዚህ ጊዜ፣ የ US Food and Drug Administration (FDA፣ የአሜሪካ የምግብ እና መድሃኒት አስተዳደር) እድሜያቸው ከ 2 አመት በታች ለሆኑ ህጻናት ማንኛውንም የቤት ውስጥ የ COVID-19 ፈጣን የእንግዳ አካል ምርመራን አላጸደቀም ወይም አልፈቀደም። ይሁን እንጂ፣ የቤት ውስጥ ፈጣን የእንግዳ አካል ምርመራዎች እድሜያቸው ከ2 አመት በታች ለሆኑ ህጻናት ለድህረ ተጋላጭነት፣ ለማግለል እና ከበሽታ ምልክት ጋር በተያያዘ ምርመራ ለማድረግ አላማዎች በጥንቃቄ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። እድሜያቸው ከ 2 አመት በታች የሆኑ ህጻናትን ለመመርመር የወሰኑ ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች የቤት ውስጥ ፈጣን የእንግዳ አካል ምርመራን እራሳቸው እንዲሰጡ ይመከራል።

FDA እድሜያቸው ከ2 አመት በታች ለሆኑ ህጻናት በቤት ውስጥ የ COVID-19 ፈጣን የእንግዳ አካል ምርመራ ጥቅም ላይ እንዲውል ባለመፍቀዱ ወይም ባለማጽደቁ ምክንያት፣ የህክምና መመርመሪያ ቦታ (MTS) ፈቃድ የተተዉላቸው የ K-12 ትምህርት ቤቶች እና

የልጅ ተንከባካቢዎች ከ 2 አመት አመት በታች ለሆኑ ህጻናት የቤት ውስጥ ፈጣን የእንግዳ አካል ምርመራዎችን እንዲያደርጉ አይፈቅድላቸውም። የ K-12 ትምህርት ቤቶች እና የልጅ ተንከባካቢዎች የቤት ውስጥ ፈጣን የእንግዳ አካል መመርመሪያዎችን ለወላጆች ወይም ተንከባካቢዎች እንዲጠቀሙባቸው ሊሰጡ ይችላሉ።

***ይህ ዶሴ ከግል-ምርመራ በኋላ ምን መደረግ እንዳለበት መመሪያን ያቀርባል።*** ይህ ማለት በጤና እንክብካቤ አቅራቢ ያልታዘዘ ወይም ያልተሰጠ ወይም ወደ ላብራቶሪ ያልተላከ እርስዎ ራስዎ የሚያደርጉት ምርመራ ማለት ነው።

ግለ ምርመራ እየተጠቀሙ ከሆነ፣ ምርመራውን ከመጠቀምዎ በፊት የተሟላ የአምራች መመሪያዎችን ማንበብዎን ያረጋግጡ። ስለ ውጤቶችዎ ጥያቄዎች ካሉዎት የጤና እንክብካቤ አቅራቢን ያነጋግሩ። አንዳንድ ትምህርት ቤቶች እና የስራ ቦታዎች ወደ ስራ ወይም ትምህርት ቤት ለመመለስ ግለ ምርመራዎችን ሊቀበሉ ይችላሉ። ለመመለስ ዝግጁ እንደሆኑ ለመወሰን የምርመራ ውጤትዎን ከአሰሪዎ፣ ትምህርት ቤትዎ፣ ወዘተ ጋር መነጋገር አለብዎት።

የግለ ምርመራ ውጤቶችዎን (ሁለቱንም ኔጌቲቭ እና ፖዘቲቭ) Say Yes! COVID Test Digital Assistant (ዲጂታል ረዳት) (በስፓኒሽ ቋንቋ ይገኛል) ን በመጠቀም በኦንላይን ሪፖርት ያድርጉ። ምንም እንኳን ከ Say Yes! COVID Test ፕሮግራም ምርመራዎን ባያዙም፣ ማንኛውንም ግለ ምርመራን ሪፖርት ለማድረግ ይህንን መሳሪያ መጠቀም ይችላሉ። ግለ ምርመራዎችን ሪፖርት ማድረግ በዋሽንግተን ውስጥ ያለውን የ COVID-19 ስርጭት የበለጠ እንድንረዳ ያግዘናል።

## የምርመራ ውጤትዎ ፖዘቲቭ ከሆነ

በግለ ምርመራ የምርመራ ውጤትዎ ፖዘቲቭ ከሆነ፣ በማግለል እና ለከባድ በሽታ የመጋለጥ እድልዎ ከፍተኛ ከሆነ እንዴት ህክምና እንደሚያገኙ ጨምሮ፣ እንዴት እራስዎን እና ሌሎችን እንደሚጠብቁ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት የዋሽንግተን ግዛት DOH የ COVID-19 ምርመራ ውጤትዎ ፖዘቲቭ ከሆነ ማድረግ አለብዎት የሚለውን መመሪያ ይመልከቱ። በፖዘቲቭ የምርመራ ውጤት ድጋሚ ምርመራ ማድረግ አይመከርም። ስለ ፖዘቲቭ የምርመራ ውጤትዎ ለጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ይንገሩ እና በህመምዎ ወቅት ከእነርሱ ጋር ይነጋገሩ። ጥያቄዎች ካለዎት እና የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ማግኘት ካልቻሉ፣ ወደ WA DOH የስልክ መስመር በ1-800-525-0127 ይደውሉ።

በ COVID-19 ቴራፒዩቲክስ (ህክምናዎች እና መድሃኒቶች) በጊዜ ጣልቃ መግባት በጣም በከባድ ህመም የመጠቃት ከፍተኛ ዕድል ላላቸው በ COVID-19 የተያዙ ሰዎች የከባድ ህመም እና ሆስፒታል የመግባት ስጋትን ሊቀንስ ይችላል። በጠና የመታመም እድላቸው ከፍተኛ የሆኑ ሰዎች (በእድሜያቸው 50 አመት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ፣ በእድሜያቸው በመግፋቱ ከፍተኛ የመጋለጥ እድል አላቸው)፣ ያልተከተቡ ወይም ክትባታቸው ወቅታዊ ያልሆነ ሰዎች፣ እና እንደ ደካማ የበሽታ መከላከያ ስርዐት ያሉ፣ አንዳንድ የጤና እክል ያለባቸው ህጻናት እና አዋቂዎች። ብቁ ሊሆኑ እንደሚችሉ ካሰቡ፣ ለ COVID-19 ቴራፒዩቲክስ (PrEP (የቅድመ ተጋላጭነት መከላከያ)፣ ሞኖክሎናል አንቲቦዲዎች ወይም በአፍ የሚወሰዱ ጸረ ቫይረሶች) ብቁነትዎን እንዲወስኑልዎት እባክዎ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ያነጋግሩ። **አይዘንጉ፦ የመጀመሪያዎቹ ምልክቶች ከታዩ በኋላ ውጤታማ እንዲሆን ህክምናው በቀናት ውስጥ መጀመር አለበት።**

ነጻ የቴሌሄልዝ መርጃዎችን ለማግኘት ከፈለጉ፣ እባክዎ የ COVID-19 ህክምና ነጻ ቴሌሄልዝ (በስፓኒሽ ይገኛል) የሚለውን ይጎብኙ እና ቀጠሮ ለማስያዝ መመሪያዎቹን ይከተሉ። ለእርስዎ እና ለጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ በልዩ የ COVID-19 ህክምናዎች ጋር በተገናኘ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የ DOH ድረገጽ (ተጨማሪ ቋንቋዎች ይገኛሉ) የሚለውን ይጎብኙ።

በለይቶ ማቆያ ዙሪያ እርዳታ ከፈለጉ፣ ለምሳሌ ምግብ፣ የግል እንክብካቤ መሳሪያዎች፣ ወይም ሌሎች ፍላጎቶች፣ ፖዘቲቭ የምርመራ ውጤትዎን ሪፖርት ለማድረግ እና ከ Care Connect ጋር ለመነጋገር እንዲጠይቁ፣ ወይም የእርስዎን Care Connect (ተጨማሪ ቋንቋዎች ይገኛሉ) ማዕከል ለማግኘት ወደ WA DOH የስልክ መስመር በ 1-800-525-0127 መደወል ይችላሉ። በለይቶ ማቆያ ዙሪያ እርዳታ ከፈለጉ፣ እርዳታ የማግኘት መዘግየቶችን ለመከላከል እባክዎ የምርመራ ውጤትዎን በስልክ መስመር ሪፖርት ያድርጉ።

ለቅርብ ንክኪዎችዎ ለ COVID-19 ተጋልጠው ሊሆን እንደሚችሉ ይንገሯቸው እና COVID-19 ያለበት ሰው ጋር ከተጋለጡ ምን ማድረግ አለብዎት (ተጨማሪ ቋንቋዎች ይገኛሉ) የሚለውን ይላኩላቸው። በአጠቃላይ የቅርብ ግንኙነት ማለት በ COVID-19 ካለበት ሰው በ 6 ጫማ ርቀት ውስጥ ቢያንስ ለ15 አማካይ ደቂቃዎች ወይም ከዛ በላይ በ24-ሰአት ጊዜ ውስጥ ቆይተዋል ማለት ነው። ይሁን እንጂ የመጋለጥ እድልን የሚጨምሩ ሁኔታዎች ላይ ከነበሩ ለምሳሌ፦ የታፈኑ ቦታዎች፣ በቂ ያልሆነ የአየር ዝውውር ባለባቸው ቦታዎች ወይም ሰዎች እንደ ጩኸት ወይም መዝሙር ያሉ ተግባራትን በሚያከናውኑባቸው ቦታዎች ላይ ከሆኑ ከእርስዎ ከ6 ጫማ በላይ ቢርቅም አሁንም እርስዎ ሊጋለጡ የሚችሉበት አደጋ አሁንም አለ ። ማናቸውንም የበሽታ ምልክቶች ከማየትዎ በፊት ከ 48 ሰዓታት (ወይም ከ 2 ቀናት) ጀምሮ እና ምልክቶች ከታዩ በኋላ ቢያንስ ለ10 ቀናት COVID-19 ን ማሰራጨት ይችላሉ። የበሽታ ምልክቶች ካልታዩ ነገር ግን በ COVID-19 ፖዘቲቭ የምርመራ ውጤት ካለዎ፣ ፖዘቲቭ የምርመራ ውጤት ከማግኘትዎ በፊት ከ48 ሰአታት (ወይም ከ2 ቀናት)

ጀምሮ እና ፖዘቲቭ የምርመራ ውጤት ካገኙ ከ 10 ቀናት በኋላ COVID-19 ን አሰራጭተው ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ አሁንም ምልክቶችን በማየትዎ ወይም በጠና በመታመምዎ፣ ወይም የበሽታ መከላከል አቅም ባለመኖርዎ ምክንያት፣ የመገለል ጊዜዎ ከ10 ቀናት በላይ ከሆነ፣ የመገለል ጊዜዎ ሲያበቃ እንደ አስተላላፊ ይቆጠራሉ። የቅርብ ግንኙነቶችዎ ለ COVID-19 ተጋልጠው እንደሆነ በማሳወቅ፣ ሁሉም ሰው እንዲጠበቅ እየረዱ ነው።

WA Notify (WA ማሳወቂያ) (ተጨማሪ ቋንቋዎች ይገኛሉ) የሚለውን ከተጠቀሙ እና በግለ ምርመራ ወቅት የ COVID-19 የምርመራ ውጤትዎ ፖዘቲቭ ከሆነ፣ እርስዎ ያጋለጡዋቸውን ሌሎች ተጠቃሚዎችን ስምዎ ሳይገለጽ ለማስጠንቀቅ የማረጋገጫ ኮድ በመጠየቅ እና ውጤትዎን በመተግበሪያው በማረጋገጥ WA Notify ን መጠቀም ይችላሉ። ይህ ምናልባት ተጋልጠው ሊሆን የሚችሉ መተግበሪያውን ለሚጠቀሙ ሰዎች ያሳውቃቸዋል ስለዚህ እራሳቸውን እና በዙሪያቸው ያሉትን ሰዎች ለመጠበቅ ጥንቃቄዎችን ሊወስዱ ይችላሉ። WA Notify ን ሲጠቀሙ ምንም አይነት ግላዊ ወይም ሊለይ የሚችል መረጃ አይሰበስብም ወይም አይጋራም። የማረጋገጫ ኮድ ለመጠየቅ፦

1. የሞባይል ስልክዎን በመጠቀም (Android ወይም iPhone) QR ኮድን ስካን ያድርጉት ወይም የማረጋገጫ ኮድ ይጠይቁ (እንግሊዘኛ ብቻ)፦

2. WA Notify የሚጠቀመውን መሳሪያዎን ስልክ ቁጥር እና አወንታዊ የ COVID-19 ምርመራ ውጤት ያገኙበትን ቀን ያስገቡ።
3. “Continue (ቀጥል)” የሚለውን ይምረጡ።

በ WA Notify ውስጥ የማረጋገጫ ኮድ መጠየቅ ካልቻሉ የግዛቱን COVID-19 ነጻ የስልክ መስመር መደወል አለባችሁ፣ 1-800-525-0127፣ በመቀጠል # ን ይጫኑ እና እርስዎ የ WA Notify ተጠቃሚ መሆንዎን ለቀጥታ መስመር ሰራተኞች ያሳውቁ። የቀጥታ የስልክ መስመሩ ሰራተኞች ተጋላጭ ሊሆኑ የሚችሉ ሌሎች የ WA Notify ተጠቃሚዎችን እንዲያነቁ መጠቀም የሚችሉትን የማረጋገጫ ሊንክ ሊሰጡዎች ይችላሉ።

ለበለጠ መረጃ እባክዎ በ WANotify.org (ተጨማሪ ቋንቋዎች ይገኛሉ) ላይ “በግለ ምርመራ የ COVID-19 ምርመራ ውጤትዎ ፖዘቲቭ ከሆነ ለሌሎች እንዴት ያሳውቃሉ”(ተጨማሪ ቋንቋዎች ይገኛሉ)የሚለውን ክፍል ይጎብኙ። ስለ WA Notify፣ ወደ ስልክዎ እንዴት ማከል እንደሚችሉ ጨምሮ የበለጠ ማወቅ ከፈለጉ፣ WANotify.org ን (ተጨማሪ ቋንቋዎች ይገኛሉ) ይጎብኙ።

## የምርመራ ውጤትዎ ኔጌቲቭ ከሆነ

ኔጌቲቭ የምርመራ ውጤት ማለት SARS-CoV-2፣ COVID-19 የሚያስከትለው ቫይረስ፣ በዚያ ጊዜ በምርመራው አልተገኘም ማለት ነው።

ተከታታይ ምርመራ አንድ ሰው ብዙ ጊዜ ሲመረመር ማለት ነው፣ ለምሳሌ በየጥቂት ቀናቱ። በተደጋጋሚ በመመርመር፣ COVID-19 ን በበለጠ በፍጥነት ማግኘት እና የኢንፌክሽን ስርጭቱን መቀነስ ይችላሉ። የግለ ስብስብ መሳሪያዎች ብዙ ጊዜ ከሁለተኛው ምርመራ ጋር የሚመጡ ሲሆኑ በተከታታይ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የተዘጋጁ ናቸው። የመጀመሪያው ግለ ምርመራዎ ኔጌቲቭ ከሆነ፣ ለተከታታይ ምርመራ የአምራቹን መመሪያዎች መከተል አለብዎት። እነዚህ ምርመራ በሶስት ቀናት ውስጥ ቢያንስ ሁለት ጊዜ፣ ቢያንስ ለ24 ሰዐታት ውስጥ እና በምርመራዎች መካከል ከ48 ሰዐታት ባልበለጠ ጊዜ እንዲከናወኑ ይጠይቃሉ። ስለ ምርመራ ውጤቶችዎ ወይም ተከታታይ ምርመራዎችዎ ጥያቄዎች ካሉዎት የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ያነጋግሩ።

በቤት ውስጥ የሚደረግ የ COVID-19 እንግዳ አካል ምርመራ ኔጌቲቭ ውጤት አንዳንድ ጊዜ “የተሳሳተ ኔጌቲቭ” ውጤት ሊሆን ይችላል። ይህ ማለት ምርመራው ከአፍንጫዎ በተወሰደው የናሙና ጥጥ ውስጥ የነበረውን የ SARS-CoV-2 ቫይረስ አላገኘም ማለት ነው። የ COVID-19 ምልክቶች ካለብዎ ወይም ለ COVID-19 ኢንፌክሽን የመጋለጥ እድልዎ ከፍተኛ ከሆነ (ለምሳሌ የ COVID-19 የማህበረሰብ ደረጃ (በስፓኒሽ ይገኛል) ከፍተኛ በሆነበት አካባቢ መሆን ወይም COVID-19 ላለበት ሰው ተጋልጠው ከነበረ) ተደጋጋሚ ምርመራ ይመከራል፦

- መጀመሪያ ላይ ኔጌቲቭ የምርመራ ውጤት ካገኙ እና የ COVID-19 ምልክቶች ካለብዎ፣ ምልክቶቹ ከታዩ በኋላ በየ 24-48 ሰአታቱ ቢያንስ በአምስት ቀናት ውስጥ እንደገና ይመርመሩ።
- የ COVID-19 ምልክቶች ከሌለብዎት እና ለ COVID-19 ተጋልጠው ከነበረ፣ ከመጀመሪያው ኔጌቲቭ የምርመራ ውጤት በኋላ ከ 24-48 ባሉት ሰአታት በእንግዳ አካል ምርመራ እንደገና ይመርመሩ። ሁለተኛዉ ምርመራ ነገቲቭ ከሆነ ነገር ግን የ COVID-19 ስጋቶች ካሉ ከሁለተኛው ነገቲቭ ምርመራ በኋላ በ 24-48 ሰአታት ውስጥ እንደገና መመርመር ይችላሉ፡ በድምሩ ቢያንስ 3 ምርመራዎች። በአንቲጅን ምርመራ 3 ግዜ ለመመርመር በቂ አቅርቦት ከሌለዎት ባለዎት አቅርቦት እና ለእርስዎ እና በአከባቢዎ ላሉ ሰዎች ተጋላጭነት ደረጃ ላይ በመመርኮዝ በትንሹ መመርመር ተቀባይነት አለው።
- በድጋሚ የተደረጉት የምርመራ ውጤቶች ኔጌቲቭ ከሆኑ ነገር ግን COVID-19 ሊኖርብዎት እንደሚችል ስጋትዎ ከቀጠለ፣ የእንግዳ አካልን በመጠቀም እንደገና ለመመርመር ሊመርጡ ይችላሉ፣ የላብራቶሪ ሞለኪውላርን መሰረት ያደረገ ምርመራ ማድረግን ግምት ውስጥ ያስገቡ፣ ወይም የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር ይደውሉ።

ለበለጠ መረጃ የ DOH የጤና እንክብካቤ ላልሆኑ ቅንብሮች የበሽታ ምልክት ውሳኔ ንድፍ እና ህብረተሰቡ (ተጨማሪ ቋንቋዎች ይገኛሉ) የሚለውን ይመልከቱ።

COVID-19 ላለበት ሰው ተጋልጠው ከነበረ እና ተከታታይ የምርመራ ውጤትዎ ኔጌቲቭ ከሆነ፣ በ COVID-19 ለለበት ሰው ከተጋለጡ ምን ማድረግ አለብዎት (ተጨማሪ ቋንቋዎች ይገኛሉ) በሚለው ውስጥ ያለውን መመሪያ መከተልዎን ይቀጥሉ።

## የእርስዎ ውጤት ልክ ያልሆነ ወይም ስህተት ካሳየ

አንዳንድ ጊዜ ውጤቶቹ ግልጽ አይደሉም ወይም ይህ ነው ለማለት የማይቻል ናቸው፣ እና የምርመራ ውጤትዎ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ መሆኑን ሊነግርዎት አይችልም። ትክክለኛ ያልሆኑ ውጤቶች በብዙ ምክንያቶች ሊከሰቱ ይችላሉ፣ ለምሳሌ ናሙናዎ በትክክል ተሰብስቦ ላይሆን ይችላል ወይም የግለ ስብስብ የምርመራ መሳሪያው ተበላሽቶ ሊሆን ይችላል። ልክ ያልሆኑ የምርመራ ውጤቶች እምብዛም ናቸው ነገር ግን ሊከሰቱ ይችላሉ።

በግል-ምርመራው ላይ ያለው ማሳያ ልክ ያልሆነ ውጤት ወይም የምርመራ ስህተት ካሳየ ምርመራው በትክክል አልሰራም። ይህ ከሆነ፣ ሌላ ምርመራ ካለ፣ ምርመራውን በአዲስ የምርመራ መሳሪያ አንድ ጊዜ ይድገሙ። ሁለተኛው ውጤት አሁንም ትክክል ካልሆነ፣ መመሪያዎቹን ይመልከቱ እና ለእርዳታ የአምራቹን ያነጋግሩ። እንዲሁም ከጤና እንክብካቤ አቅራቢ ወይም ከ የህብረተሰብ የጤና ምርመራ ቦታ (ተጨማሪ ቋንቋዎች ይገኛሉ) ምርመራ ማግኘት ይችላሉ።

## ተጨማሪ የ COVID-19 መረጃ እና ግብዓቶች

በወቅታዊ የ COVID-19 ሁኔታ በዋሽንግተን (እንግሊዝኛ ብቻ)፣ የአገረ ገዢ Inslee አዋጆች (በቻይንኛ (ቀላል)፣ ኮሪያኛ፣ ሩሲያኛ፣ ስፓኒሽኛ እና ቬትናምኛ ይገኛል –በድረገጹ ላይ ካለው ዝርዝር ይምረጡ)፣ ምልክቶች (በተጨማሪ ቋንቋዎች ይገኛል – በቻይንኛ (ቀላል)፣ ኮሪያኛ፣ ስፓኒሽኛ፣ ቬትንሃምኛ)፣ እንዴት ይሰራጫል (በተጨማሪ ቋንቋዎች ይገኛል – በቻይንኛ (ቀላል)፣ ኮሪያኛ፣ ስፓኒሽኛ፣ ቬትንሃምኛ)፣ ሰዎች እንዴት እና መቼ መመርመር አለባቸው (በተጨማሪ ቋንቋዎች ይገኛል)፣ እና ክትባቶችን የት ያገኛሉ (በተጨማሪ ቋንቋዎች ይገኛል) እንደዘመኑ ይቆዩ። ለተጨማሪ መረጃ በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎቻችንን (እንግሊዘኛ ብቻ) የሚለውን ይመልከቱ።

የአንድ ግለሰብ ዘር/ብሔር ወይም ዜግነት በራሱ በ COVID-19 የመያዝ ዕድላቸውን ከፍ እንዲል አያደርግም። ሆኖም ግን ከጥናትና ምርምር የተገኙ መረጃዎች ነጭ ያልሆኑ ሰዎች የሚገኙባቸው ማኅበረሰቦች በ COVID-19 ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰባቸው እንደሆነ ያሳያሉ። ይህ ሊሆን የቻለው ከዘረኝነት እና በተለይም አንዳንድ ራሳቸውን እና ማኅበረሰባቸውን ለመጠበቅ እንዳይችሉ ከሚያደርግ ተቋማዊ ከሆነ ዘረኝነት የተነሣ ነው። መገለል በሽታውን ለመቋቋም አይረዳም (እንግሊዝኛ ብቻ)። ወሬዎች እና የተሳሳቱ መረጃዎች እንዳይሰራጩ ለመከላከል ትክክለኛውን መረጃ ብቻ ለሌሎች ያጋሩ።

- የ WA State Department of Health (የ WA ግዛት የጤና መምሪያ) የኮሮና ቫይረስ ምላሽ (COVID-19) (ተጨማሪ ቋንቋዎች ይገኛሉ)

- [የእርስዎን የአካባቢ ጤና መምሪያ ወይም ዲስትሪክት ያግኙ](#) (እንግሊዝኛ ብቻ)
- [የ Centers for Disease Control & Prevention (CDC፣ የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከል) ኮሮና ቫይረስ (COVID-19)](#) (ተጨማሪ ቋንቋዎች ይገኛሉ – ቻይንኛ (ቀላል)፣ ኮሪያኛ፣ ስፓኒሽ፣ ቬትናምኛ)

**ተጨማሪ ጥያቄዎች አልዎት?** ወደ COVID-19 መረጃ ቀጥታ መስመራችን በ **1-800-525-0127 ይደውሉ።** የቀጥታ መስመር ሰዓታት፦

- ሰኞ ከ 6 a.m. እስከ 10 p.m.
- ከማክሰኞ እስከ እሁድ ከ6 a.m. እስከ 6 p.m.
- [የሚከበሩ የግዛት በአላት](#) (እንግሊዘኛ ብቻ) ከ 6 a.m. እስከ 6 p.m.

ለአስተርጓሚ አገልግሎቶች፣ መልስ ሲሰጥዎት **# ይጫኑ** እና **የእርስዎን ቋንቋ ስሙን ይናገሩ**። ስለ ራስዎ ጤና ወይም የምርመራ ጥትያቄዎች፣ እባክዎ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ያነጋግሩ።

ይህን ሰነድ በሌላ ቅርጸት ለመጠየቅ፣ በ 1-800-525-0127 ላይ ይደውሉ። መስማት የተሳናቸው ወይም መስማት የሚቸገሩ ደንበኞች፣ እባክዎ በስልክ ቁጥር 711 ([Washington Relay](#)) (እንግሊዘኛ ብቻ) ይደውሉ ወይም ኢሜይል ወደ civil.rights@doh.wa.gov ይላኩ።